2023

የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስትያን አነሳስ



አዘጋጅ፡ እስክንድር ብርሃኑ

Contents

የአድቬንቲስ ቤተክርስቲያን ከመነሳቷ በፊት ምን ምን ትንቢቶች ተፈጽመው ነበር 4

የሊዝበን የመሬት መንቀጥቀጥ.....6

ጋዜጦች በወቅቱ ምን ይሉ ነበር 7

የፀሀይ መጨለም እና ወደ ደም መለወጥ ሌላው ምልክት.....8

ሌላኛው ምልክት (ሁለተኛ ምልክት).....8

የዳግም ምፅአት ሰባኪዎች 9

ኤድዋርድ አርቪን ታሪክ (Edward irvin).....9

የጆሴፍ ዎልፍ ታሪክ (Joseph Wolfe).....10

የዳግም ምፅአት ሰባኪዎች አነሳስ (Advent Movement).....10

ዊሊያም ሚለር (William Miller) 10

እየሩሳሌም መቅደሱም ቅጥሩም እንዲገነባ ትእዛዝ የወጣበት ዓመታት.....12

አዲሱ አተረጓጎም 15

ጆሽዋ ሄምስ (Joshua Himes).....16

ሄራም ኤድሰን (Hiram Edson) 1806-1882 16

Hiram Edson (ሄርማ ኤድሰን አጭር ታሪክ) 17

የሰባተኛ ቀን አድቪቲስት ቤተክርስቲያን ፈር ቀዳጆች/ፋና ወጊዎች (Pionneers).....18

John Nevins Adrews (ጆን ኔቪስ አንድሪው) 19

ጆሴፍ ቤት 20

Sylvester Bliss (1844-1863) 21

DANLE T BOURDEAU (1835-1905).....22

John Byington 23

Merritt E.Cornell (1827-1893).....24

Owen Resell Loomis Crosier (1820-1913) 25

Charles Fitch (1805-1844) 26

Stephen is Haskell 27

John Norton Lough brorough (1832-1924) 29

William Miller (ዊሊያም ሚለር).....30

Thomas M. Preble 31
ቶማስ ኤም ፕሬብል 31
Uriah Smith (1832-1903).....32
ዩሪያ ስሚዝ.....32
Ellen.G.White 33
James Springer White (1821-1881).....34
ጀምስ ስፕሪንገር ዋይት.....34
Alongo T. Jones (1850-1923).....35
Dr. Ellet J.Wagner.....36
ዶ/ር ኤሌት ጄ ዋግነር 36
William Warren Prescott.....37
Gorge Storrs.....39

መቅድም

የዚህ ፅሑፍ ጭብጥ ዋና ትኩረት ስለ ሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን አጠቃላይ አመሰራረትና አነሳስ የተሟላ መረጃን በመረጃ አስደግፎ ማቅረብ ነው፡፡ እግዚአብሄር ይህችን ቤተክርስቲያን እንዴት አድርጎ አዳስነሳት በቂ መረጃ ይሰጣል፡፡ እንዲሁም የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅሶችን፤ የቤተክርስቲያን ታሪክንና የአለምን ታሪክ አካቶ/አጣምሮ ማስረጃ ያቀርባል፡፡ በዚህም በመጽሐፍ ቅዱሳችን ትንቢተ ዳንኤል 8፡14 ፣ ዳንኤል 12፡11-13፣ ዩሐንስ ራዕይ 19፡10፣ ዩሐንስ ራዕይ 10፡ 10-11 እንዲሁም ዩሐንስ ራዕይ 12፡17ን እንደ ዋነኛ ምንጭ እንጠቀማለን፡፡ በተጨማሪም ይህ ፅሁፍ የዩሐንስ ራዕይን ምዕራፍ 5፣6 እና 8 ታሪካዊ ዳራ አስመርኩዞ እንዴት የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን እንደተነሳች ያስረዳል፡፡

በመሆኑም ስለዚህች ቤተክርስቲያን ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚያነቡ እና የአድቬንቲስት እምነት አባላት ሆነው የቤተክርስቲያናችንን ታሪክ ለማያውቁ ሰዎች በቂ መረጃ ይሰጣል፡፡

ፅሑፉ የቤተክርስቲያንን እና የአለምን ታሪክ በማመሳከር ይህች ቤተክርስቲያን እንዴት እንደተነሳች ማረጋገጫ ያቀርባል፡፡

ይህ ፅሁፍ የተወጣጣው /የተፃፈው/

1. The prophet among you
2. Urian Smith Daniel and Revelation
3. Adventist pioneer library website ከተሰኙ ፅሑፎች ላይ ነው፡፡

የአድቬንቲስ ቤተክርስቲያን ከመነሳቷ በፊት ምን አይነት ትንቢቶች ተፈጽመው ነበር

የአድቬንቲስ ቤተክርስቲያን ከመነሳቷ በፊት ምን ምን ትንቢቶች ተፈጽመው ነበር

የነዚህ ሶስት ትንቢቶች መፈጸም የጌታችን የእየሱስ ዳግም ምፅአት መቅረቡን ያሳያል፡፡

1. የሊዝበን መሬት መንቀጥቀጥ
2. የከዋክብት መውደቅ
3. የጨረቃ መጨለም

ስለነዚህ ምልክቶች ወደፊት በጥልቀት የምንመለከተው ይሆናል፡፡ በዩሐንስ ራዕይ 5፥1-14 በጣም የሚያስደንቅ በዘመናት ሁሉ የተከሰቱትን የቤተክርስቲያን ታሪኮች በልዩ ሁኔታ ዩሐንስ አይቶ ነበር፡፡ ዩሐንስ በራዕይ የተመለከተው ምንድን ነበር?

1. በመጀመሪያ አንድ ነጭ ፈረስ ወጣ ይላል፤ የመጀመሪያውም ማህተም ሲፈታ (ይህ ወርቃማውን የቤተክርስቲያን ታሪክን ያሳያል)



2. ሁለተኛው ማህተም ሲፈታ አንድ ቀይ ፈረስ ወጣ ይላል (ይህ ቤተክርስቲያን ብዙ ዋጋ የከፈለችበት፤ ብዙ ስደት የደረሰባት ጊዜ ነበር) ይህን በቀለሙ መለየት ይቻላል በመጀመሪያ ነጭ ፈረስ ነበረ፤ ከዚያ ግን ጥቁር፡፡ ይህ የሚያሳየው መጀመሪያ ቤተክርስቲያን ንፅህናዋን ጠብቃ ከዚያ በኋላ ግን ያንን ንፅህናዋን እንዳጣች ያሳያል፡፡ የታሪክ ፀሀፊዎች እንደሚሉት ይህ ጊዜ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ100-311AD ያለው የቤተክርስቲያን ጊዜን ያሳያል፡፡

3. ሶስተኛው ማህተም ሲፈታ አንድ ጥቁር ፈረስ ወጣ ይላል (ይህ የቤተክርስቲያን የጨለማው ዘመን ይባላል) መፅሀፍ ቅዱስ የማይነበብበት ጊዜ ነበር፡፡ ለ1260 አመታት ቤተክርስቲያን በሮም ካቶሊክ አማካኝነት ስደት ያጋጠማት ጊዜ ነበር፡፡ የመበላሸቱ ሁኔታ ምን ያህል ፈጣን እንደሆነ የቀለሙ ልዩነት ያሳያል፤ጥቁር ፈረስ የነጭ ፈረስ ተቃራኒ ነው፤ በጣም ትልቅ ጨለማ እና የሞራል መበላሸት በቤተክርስቲያን ውስጥ በዚህ ምልክት ይገለፃል፡፡ ይህ ጊዜ ቆንስጣንቲን **(Constantine)** ከነገሰበት ጊዜ እና የጳጳሳዊው ስርዓት በ538 የጀመረበት ጊዜ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በቤተክርስቲያን የተሳሳቱ/የስህተት ትምህርቶች የገቡበት ጊዜ ነበር፡፡

4. አራተኛው ማህተም ያለ ጥርጥር የሚያሳየው ጳጳሳዊው ስርዓት ምንም አይነት ከልካይ ሳይኖረው የማሳደድ ስራውን በ538

   AD የጀመረበትን እና የተሐድሶ ሰባኪዎች ተነስተው የጳጳሳዊውን ስርዓት መበላሸት ያጋለጡበት ሰዓት/ጊዜ ነበር፡፡

5. አምስተኛውም ማህተም ሲፈታ በመሰዊያው ስር የተሰውትን ነፍሳት አየሁ ይላል፡፡ አንድ ቀን እግዚአብሔር በክርስትናቸው ምክንያት ለተሰዉ ሰዎች ፍትሕ እንደሚሰጥ ያሳያል፡፡ ልክ የቃየል ደም ወደ እግዚአብሔር እንደሚጮህ የእነዚህ ክርስቲያኖች ደም ወደ ሰማይ ይጮህል፡ ፡ የዚህ ማህተም ወቅት የሚያሳየው የጳጳሳዊውን ስርዓት ተከትሎ ተሀድሶ የጀመረበት፤ የጳጳሳዊው ስርዓት ችግር የገጠመበት እና የሮማን ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የማሳደድ ሀይሏ የታገተበት ወቅት ነበር፡፡

6. ስድስተኛው ማህተም ሲፈታ በሰማይ ታላቅ ምልክት ሆነ ይላል፡፡

   1. የምድር መናወጥ ሆነ
   2. የፀሀይ ጥቁር መሆን
   3. ጨረቃ እንደ ደም ቀይ ሆነች ይላል
   4. ከዋክብት ወደ ምድር ረገፉ ይላል ኢዩኤል፡ 2፥31፣ማቴ፡ 24፥1-10

7. ሰባተኛው ማህተም ሲፈታ በሰማይ ለግማሽ ሰዓት ፀጥታ ሆነ ይላል፡፡ ይህ የሚሆነው ክርስቶስ መላእክቶችን ይዞ ወደዚህ ምድር በሚመለስበት ሰዓት ሰማይ ባዶ ስለሚሆን በዚህ ምክንያት ፀጥታ በሰማይ ስለሚሆን ነው፡፡

የሐንስ ራዕይ 6፥12-13 ይመልከቱ ተመሳሳይ ሀሳቦች በብሉይ ኪዳን ተነግረው ነበር፡፡

እነዚህ ምልክቶች የክርስቶስን ዳግም ምፅአት የሚያሳዩ ብቻ ሳይሆኑ ለቅፊታዋ ቤተክርስቲያን የተሰጣትን ከትንቢት መንፈስ ጋር ያለውን ግንኙነት ያመላክታሉ፡፡

- ትንቢቶቹ የሚያሳዩበት የትንቢት መንፈስ ስጦታም በእነዚህ ምልክቶች ማዕቀፍ ውስጥ እንደሚፈፀም ያሳያል፡፡

የሊዝበን የመሬት መንቀጥቀጥ

በዩሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 6 እና 8 ያለው የሰባቱ ማህተም ትንቢት የሚያሳየው የክርስቶስን ዳግም ምፅአት ነው።።

በተጨማሪ እነዚህ ጥቅሶች በደንብ ይመልከቱ

- ዳንኤል ምዕራፍ 2፥7
- ማቴዎስ ምዕራፍ 24 እና ማርቆስ 13
- ሉቃስ ምዕራፍ 21
- 2 ተሰሎንቄ ምዕራፍ 1፥2
- 2 ጴጥሮስ ምዕራፍ 3
- ዩሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 2 እና 3፥ 6-14 ያሉትን እነዚህ ሁሉ የክርስቶስን ዳግም ምፅአት የሚያመላክቱ ናቸው።።
- ዩሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 11፥15 (ላይ የዚህ አለም መንግስት የጌታችን የእየሱስ ክርስቶስ ሆነ) የሊዝበን መሬት መንቀጥቀጥ 1755 የተከሰተ ነው።።

1. የተከሰተው ህዳር (November) 1 ቀን ሲሆን እለቱም ቅዳሜ ነበር።።
2. የፃድቅ ቀን የሚያከብሩበት ወቅት ነበር
3. ከጠዋቱ በ3፡40 ላይ ነበር የመሬት መንቀጥቀጡ የተከሰተው
4. ከፍተኛ የሆነ እሳት እና የባህር ማዕበል ነበር
5. ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ከተማዋ ጠፍታ ነበር (የሊዝበን)
6. የመሬት መንቀጥቀጡ 200 ኪ.ሜ ድረስ የአትላንቲክን ውቅያኖስን ይዞ ንዝረቱ ይሰማ ነበር።። በዚህ የመሬት መንቀጥቀጥ 10,000 - 30,000 የሚገመት ሰው ጠፍቷል።። ይህ የመሬት መንቀጥቀጥ (የሊዝበን) በሚከሰትበት ጊዜ ያለው ታሪክ ምን ይመስል ነበር።።

- በ1755 አካባቢ በአውሮፓ እና በአሜሪካ በከፍተኛ ደረጃ ቅኝ ግዛት ይካሄድ ነበር።።
- በፈረንሳይ እና በእንግሊዝ የግዛት ጥያቄ የነበረበት ወቅት ሲሆን ይሄም ጦርነት አስከትሎ ነበር።። ወደ በኋላ አካባቢ እንደ አውስትራሊያ፣ ራሽያ፣ ፖርቹጋል እና ሌሎችም ሃገሮች ተሳትፈውበት ነበር።። በታሪክ ይህ ‹የሰባቱ ዓመታት ታሪክ› በመባል ይታወቃል።።

- በብዙ የአለማችን ክፍሎች በመሬት ይገባኛል ምክንያት ብዙ ጦርነት ይካሄድ ነበር
- በፈረንሳይ ሃገር ላይ በ1763 ተሰብስበው ስምምነት እስኪያደርጉ ድረስ ስምምነቱ የHUBERTUSBURG ስምምነት በመባል ይታወቃል፡፡

ከ1755-1763 ድረስ አለማችን በጦርነት ትታመስ ነበር፡፡ በፖለቲካው አለም ላይ አለም በራሱ መንገድ እየተጓዘ ባለበት ወቅት እግዚአብሔር ዳግም የራሱን መንገድ ይሄድ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ሰዎችን ለክርስቶስ ዳግም ምፅአት ለማዘጋጀት የራሱን ፕሮግራም የጀመረበት ጊዜ ነበር፡፡ በ18ኛው ክፍለ ዘመን ከፍተኛ የሆነ ሀይማኖታዊ መነቃቃት ነበር፡፡ ከ1730 ጀምሮ ከፍተኛ የሆነ የመንፈሳዊ ወይም የሀይማኖት እንቅስቃሴ እንደጀመረ ማየት እንችላለን፡፡

<u>ሰባኪዎች</u>፡-

1. ጆናታን ኤድዋርድ (Jonathn Eduard) በአሜሪካ የነበረ ሰባኪ
2. ዌልስያን (Welseyan) የሀይማኖት መነቃቃትን በለንደን (London) በብዙ ሰዎች ዘንድ ፈጥሯል፡፡
3. የጆርጅ ዋይት ፊልድ አገልግሎት በእንግሊዝ ኦክስፎርድ ተማሪዎች (Oxford Student)
4. በመላው አሜሪካ በሚባል ደረጃ በኒው ኤንግላንድ፣ በመካከለኛውና በደቡብ ቦታዎች በዚህ ከፍተኛ በሆነ መንፈሳዊ መነቃቃት የተነኩ ቦታዎች ነበሩ፡፡

ጋዜጦች በወቅቱ ምን ይሉ ነበር ?

የሀይማኖት ታሪክ በአሜሪካ በሚባለው መፅሀፍ ገፅ 201 እንዲህ ይላል፡-

“ይህ መንፈሳዊ መነቃቃት መላውን አሜሪካን አዳርሶ ነበር”

The story of religions in America. P 201 ዘጀንትል መጋዚን እንደዘገበው፡፡

ሉቃስ 21፣25 እና 26 ሌላው የታሪክ ሂደት በወቅቱ ህዳሴ እና ሂውማኒዝም (Humanism) የሚባሉት ሁለት ነገሮች ተከስተዋል፡፡

- በዚህ ወቅት በመላው አውሮፓ ነዋሪዎች ወደ ዘመናዊነት የሚሸጋገሩበት ወቅት ነበር
- ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊ ለውጥ የሚደረግበት ወቅት ነበር (Social change)
- ይህ በ17ኛው ክፍለ ዘመን የተጠናቀቀ ነበር፡፡
- ከግሪክ እና ከሮም የተወሰደውን ሂውማኒዝም የሚባለው ትምህርት (ፍልስፍና) የሚያራምዱበት ወቅት ነበር፡፡

(Humanism)

- አዲስ አስተሳሰብ በአርት፣ በአርክቲክቸር፣ በፖለቲካ፣ በሳይንስ እና በስነ-ፅሁፍ ዙሪያ ያተኮረ/ያጠነጠነ ነበር።
- መሰረታዊ እምነታቸው እግዚአብሔር የለም የሚባልበት ወቅት ነበር

የፀሀይ መጨለም እና ጨረቃ ወደ ደም መለወጥ ሌላው ምልክት

- ይህ ክስተት አሜሪካውያንን በጣም ያስገረመ እና የክርስቶስ ዳግም ምፅአት በጣም እንደቀረበ የተገነዘቡበት ወቅት ነበር።
- ወቅቱ ከፍተኛ የሆነ የጦርነት አዝማሚያ የነበረበት ጊዜ ነበር። አሜሪካኖች ለነፃነት የሚያደርጉት ጦርነት የጀመረበት ወቅት ነበር። በሚያዝያ (April 19,1775) በኮንከርድ እና ሌክሲንግተን በሚባል ቦታ ላይ (Concord and Lexington)
- ለቀጣዩ ስምንት ዓመታት በአሜሪካ በጣም ችግር ነበር።
- የአሜሪካን ጦር ከፍተኛ ጉዳት/ሽንፈት የደረሰበት/ያስተናገደበት ወቅት ስለነበር በእንግሊዝ ሀይቆች አካባቢ የዚህን ትንቢት መፈጸም አስመልክቶ የየል ኮሌጅ ፕሬዝዳንት የሆነው ሰው ስለ ድርጊቱ ሲናገር "የፍርድ ቀን በደጅ ቀርቧል" ብሎ አስታውቆ ነበር። በ1781 የኮንግሪሽናል ቤተክርስቲያን አማኝ የሆነው ሳሙኤል ጊትቺል የተባለው ሰው (Samuel Gatchel) "የመጨረሻው ዘመን ምልክት" ብሎ ፅፎ ነበር። እዩኤል 3፥15
- ፀሀይ ወደ ጥቁር ትለወጣለች ጨረቃም ወደ ደም ታላቁ የሚያስፈራው የሚያስጨንቀው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ በፊት እዩኤል 2፥31

ሌላኛው ምልክት (ሁለተኛ ምልክት)

የከዋክብት መርገፍ፡- ይህ ምልክት ለመፈጸም ቢያንስ የ50 ዓመታት ክፍተት ነበር። ከመጀመሪያው ምልክት በኋላ ይህ የከዋክብት መርገፍ ከስድስተኛ ማህተም ጋር ግንኙነት አለው። ዩሐንስ ራዕይ 6፥ 12-17

ይህ ምልክት በሚፈፀምበት ወቅት የአለም ታሪክ ምን ይመስል ነበር ወይም አለም በምን ሁኔታ ውስጥ ነበር

ወቅቱ ክሪትሲዝም የሚባለው ፍልስፍና መሰረት የጣለበት ወቅት ነበር። በሊዮፖልድ ቫን ራንኪ (Leopold Van Ranke)

- በ1821 ምድር ላይ Champolism ተጀምሮ ነበር
- ዘመናዊ የሆነ የከርሰ ምድር ጥናት የጀመረበት ወቅት ነበር በ1830-33 በቻርልስ ሌይል (Charles Lyell)
- ኤሌክትሪካል ሳይንስ የጀመረበት ወቅት ነበር (Electrical Science)
- የሴል ቲዎሪ የጀመረበት ወቅት ነበር። (Cell theory) በማቲያስ እና በጓደኞቹ በጀርመን
- በ1832 በሳሙኤል ኤፍ ሞሪስ ኤሌክትሪካል ቴሌግራም የጀመረበት ወቅት ነበር።
- በ1833 በእንግሊዝ ሃገር ባሮችን ነፃ የሚያወጣ ህግ አውጥተው ነበር።
- እንግሊዝ ህፃናትን ያለ እድሜያቸው እንዳይሰሩ ህግ ያወጣችበት ወቅት ነበር (Child Labor)
- የቱርክ ወታደራዊ ሀይል የግብፅን ወታደራዊ ሀይል ያሸነፈበት ወቅት ነበር።
- በ1833 ጀርመን በርሊን ለመጀመሪያ ጊዜ በኮሌጅ ውስጥ ዘርን መሰረት ያላደረገ ትምህርት መስጠት የጀመረበት ወቅት ነበር (ጥቁር ከነጭ ጋር ተደባልቆ ትምህርት መስጠት የጀመረበት ወቅት ነበር)
- የሞርሞን እምነት የጀመረበት ወቅት ነበር በጆሴፍ ስሚዝ (Joseph Smith)

የዳግም ምፅአት ሰባኪዎች

1. ማኑኤል ዲላኩዊዝ (Manel De Lacuiz)
2. ኤድዋርድ ኢርቪን (Edward Irvin)
3. ጆሴፍ ዎልፍ (Joseph Wolf)
4. ሎቪስ ጓሰን Lovis Gaussen

ኤድዋርድ ኢርቪን ታሪክ (Edward Irvin)

- በስኮትላንድ ነው የተወለደው።ልቡ የተነካው እና የሰለጠነው በማኔል ዲ ላኩንዝ (Manel de Lacunz) ነው ማለት ይቻላል።

በእንግሊዝ ከተማ ይኖር ነበር፤ ስለክርስቶስ በክብር ወደዚህ አለም መመለስ በማንበብ በጣም ልቡ ተነክቶ ነበር። የተማረ እና ለሀይማኖቱ ቅንአት የነበረው ሰው ነው። በለንደን (London) ከተማ ውስጥ ቀደም ብሎ የክርስቶስን ዳግም ምፅአት በመስበክ ይታወቅ ነበር።ሰባኪያን ከ10000 እስከ 15000 ሰዎችን በመሰብሰብ ይሰበኩ ነበር። ታዲያ ኤድዋርድ ወደ አገልግሎቱ መጨረሻ ላይ በሀሰት ትምህርት አስተማሪነት ተከሶ ነበር።

የጆሴፍ ዎልፍ ታሪክ (Joseph Wolfe)

በ1844 ከዩንቨርስቲ ኦፍ ጀኔቫ (University of Geneva) ተመርቆ ነበር። የተቀባ አገልጋይ ነው። ለ12 ዓመታት በፓስተርነት አገልግሎት ላይ ነበር። ትንቢተ ዳንኤልን ለየት ባለ ሁኔታ ያነብ ነበር፤ ሰዎች በጣም ሲቃወሙት ስለነበር የትንቢተ ዳንኤልን መፅሀፍ በትምህርት መልክ ፅፎ አዘጋጅቶ ነበር፤ ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ ሁለት የአለም ታሪክ ላይ ያለውን አተኩሮ ይገልጥ ነበር።

የዳግም ምፅአት ሰባኪዎች አነሳስ (Advent Movement)

የክርስቶስ ዳግም ምፅአት እንቅስቃሴ በአውሮፓ እና በሌሎች ሃገሮች በጣም ይሰበክ ነበር፤ አሜሪካንም ጨምሮ በ18 እና በ19ኛው ክፍለ ዘመን በመፅሀፍ ቅዱስ ላይ ያለውን ትንቢት ለማወቅ ወይም ለመገንዘብ ሰዎች ከፍተኛ ጥረት የሚያደርጉበት ወቅት ነበር። በዚህም ምክንያት የተለያዩ መፅሀፍት የተለያዩ እጥር ብለው የሚፃፉ ፅሁፎችን በስፋት ያዘጋጁ ነበር።

በዳንኤል ትንቢት ላይ ያለውን 1200 እና 2300 ዓመት ትንቢት ላይ አተኩረው እንዲሁም በጳጳሳዊው ስርዓት ላይ አተኩረው ይፅፉ ነበር፤ የኦቶማን ኤምፓየርን ጨምሮ ማለት ነው።

ዊሊያም ሚለር (William Miller)

- የባብቲስት ቤተክርስቲያን አባል ነበር
- ገበሬ ነበር
- የክርስቶስን ዳግም ምፅአት የሰበከ ሰው ነው
- ዳንኤል ምዕራፍ 8፣14ን በጥልቀት ያጠና ነበር
- በኦክቶበር 22, 1844 ላይ የሰማያዊው ቤተክርስቲያን ይነፃል ብሎ ያስተምር ነበር
- የክርስቶስ ዳግም ምፅአት በቅርቡ ይሆናል ብሎ ያምን ነበር። ዊሊያም ሚለር (William Miller) እስከ 1831 የፍሪሜሶን አባል የነበረ ነው። (Freemason) በ1831 ከዚህ

ሚስጥራዊ ድርጅት በግልጽ ለቋል፡፡ በ1833 ዊሊያም ሚለር ለጓደኛው የፃፈው ደብዳቤ እንደሚያሳየው ፍሪሜሶን የሚባለው ተቋም በጣም መጥፎ (evil) እንደሆነ ገልጿል፡፡

- በታህሳስ 20, 1949 የሞተ ሲሆን፣ እስከሞተበት ጊዜ ድረስ የክርስቶስ ዳግም ምፅአት በቅርቡ እንደሚሆን ያምን ነበር፡፡
- ዊሊያም ሚለር በኒዮርክ ሎው ሐምተን ተቀብሯል፡፡
- የዊሊያም መኖሪያ ቤት እንደ ቅርስ ተመዝግቧል፡፡ እንደ ሙዚየምም የሚታይ ቤት ሆኗል፡፡ የዊሊያም ሚለር ትምህርት ለሰባተኛ ቀን አድቬቲስት ቤተክርስቲያን ትምህርት መሰረት ጥሏል፡፡

ዊሊያም ሚለር መፅሀፍ ቅዱስ ከሁሉም አይነት ትምህርቶች ይበልጣል ብሎ ያምናል፤ ሁሉም የመጽሀፍ ቅዱስ ጥቅሶች አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያምናል፡፡ ይህ እንቅስቃሴ በመጨረሻ ላይ በክርስቶስ ዳግም ምፅአት የተደመደመ ሳይሆን በተስፋ መቁረጥ የተደመደመ ነበር፡፡ አስተማሪዎች፣ ጠበቃዎች፣ የኮሌጅ ፕሬዝዳንቶች እና ሌሎችም ሰዎች የክርስቶስን ዳግም ምፅአት በመስበክ በጣም ተጠምደው ነበር፡፡

የባብቲስት ቤተክርስቲያን አባል የነበረና እንዲሁም በግብርና የሚተዳደር ሰው ሲሆን፣ የዳንኤልን ትንቢት በማጥናት፤ በተለይ በምዕራፍ ስምንት የቤተመቅደሱን መቀደስ በተመለከተ የተሰጠውን ትንቢት ትኩረት ሰጥቶ የክርስቶስ ዳግም ምፅአት እንደቀረበ ያስተምር ነበር፡፡ ዳንኤል 8፥14

በታሪክ ስናጠና የክርስቶስ ዳግም ምፅአት መቅረቡን በወቅቱ ከሚያሳዩ ምልክቶች የፈረንሳይ አብዮት ዋነኛው ነበር፡፡ በአለማችን ላይ ዊሊያም ሚለር ምክንያት ሆኖ ብዙዎች የአለም ሰዎች የሱን ሃሳብ በመመርኮዝ መፅሀፍ ቅዱስን ያጠኑ ነበር፡፡

በዳንኤል ላይ የተነገረው 1200 ትንቢት አስተውለው ነበር፤ 1798 የዚህ ትንቢት ፍፃሜ (1200) እንደሆነም አስተውለው ነበር፡፡

በዳንኤል 8፥14 ላይ የተነገረው 2300 ትንቢት የሚያልቀው በ1844 ላይ እንደሆነም ተገንዝበው ነበር፡፡

ሕዝቅኤል 4፥6 እና ዘሁልቁ 14፥34 ትንቢቱን የፈቱበት አንዱ መሳሪያ ነው፡፡ ቤተመቅደስ የሚለው ይህች ምድር ነች በማለት እና ክርስቶስ ወደዚህ ምድር በሚመጣበት ጊዜ ይህችን ምድር በእሳት ያጣፋታል የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ዊሊያም ሚለር የጥናቱ መደምደሚያ

አድርጎት ነበር፡፡ ብዙ ሰዎችም ይህን አምነው ተከትለው ነበር፡፡ 1 ጴጥ 3፥7 ዊሊያም ሚለር 2300 በዳንኤል 8፥14 ላይ ያለውን ትንቢት በዳንኤል ምዕራፍ 9 ላይ ተመርኩዞ ፈቶት ነበር።

ለተጨማሪ ጥናት ዳንኤል ምዕራፍ 9 ያንብቡ

እየሩሳሌም መቅደሱም ቅጥሩም እንዲገነባ ትእዛዝ የወጣበት ዓመታት

1. በ536 BC በሳይረስ መቅደሱ እንዲገነባ ትእዛዙ ወጥቶ ነበር፡፡
2. በ519 BC በዳሪዮስ መቅደሱ እንዲያልቅ የወጣ ትዕዛዝ፡፡
3. በ457 BC በአርቲክሰስ በፐርሺያ ንጉስ መቅደሱም እንዲሁም ቅጥሩ እንዲገነባ የወጣው ትእዛዝ
4. በ444 BC በነህምያ ጊዜ የእየሩሳሌምን ቅጥሮች እንዲጨርሱ የወጣው ትእዛዝ

ዊሊያም ሚለር እንደሚለው መቅደሱ እና ቅጥሩ እንዲሰራ ትእዛዝ የወጣበትን ዓመት በ457 BC የሚለውን ተጠቅሟል፡ ዳንኤል ምዕራፍ 9፥1-10


የባብቲስት እማኝ የነበረው ዊሊያም ሚለር እንቅስቃሴ በታላቅ ተስፋ መቁረጥ የተበተነ ነበር፤ ምክንያቱም ክርስቶስ 1844 ላይ ሳይመለስ ስለቀረ ክርስቶስን ተሰብስበው ሲጠብቁ የነበሩ፣ ከተለያዩ እምነት የመጡት ሁሉ ወደ መጡበት እንደተመለሱ ታሪክ ያሳያል፡፡

1. ከዚህ ታላቅ ተስፋ መቁረጥ በኋላ የተለያዩ ሰዎች ተስፋ ባለመቁረጥ መፅሀፍ ቅዱስን በጥልቀት ማጥናት ጀመሩ፡፡ በተለይ ስለ ቤተ መቅደሱ የሚያወራውን የዕብራዊያንን መፅሀፍ፤ ዕብራዊያን ምዕራፍ 8፥9-10 በጥልቀት አጠኑት፡፡
2. በሱባኤውም እኩሌታ (በሳምንቱ ግማሽ) መሲሁ ቁርባኑን እና መስዋእቱን ያስቀራል፡፡
3. በእርኩሰትም ጫፍ ላይ አጥፊው ይመጣል፡፡ ማቴ 24፥15-20 የእየሩሳሌም በሮም መጥፋትን ያሳያል፤ እንደ ትንቢቱ በ70AD ላይ...

   /ታላቁ ተጋድሎ የሚለውን የኤለንጅዋይት መፅሀፍ የመጀመሪያውን ምዕራፍ ለበለጠ መረጃ ያንብቡት/

4. እስከ ተቆረጠውም ፍፃሜ ድረስ መቅሰፍት በአጥፊው ላይ ይፈሳል፡፡

ገብርኤል ለዳንኤል በምዕራፍ 8 ላይ ባሳየው ራዕይ በምእራፍ ዘጠኝ ላይ በደንብ አብራርቶለታል፡፡ ዊሊያም ሚለር ይሄንን ከመፅሀፍ ቅዱስ በጥልቀት በማጥናት ነበር የክርስቶስ ዳግም ምፅአት በ1844 ነው የሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው፡፡



2300
-457
1843

+1

1844

✞ ከ2300 ላይ 457 - 1843 ይመጣል፤ ዜሮ የሚባል አመት ስለሌለ 1 ስንደምርበት 1844 ላይ እንደርሳለን (AD - BC ዓመቱ ሲለወጥ)


✞ ዊሊያም ሚለር ክርስቶስ 1844 ላይ ሳይመጣ ሲቀር እንደ ሌሎቹ ተከታዮች ተስፋ ቆርጦ ነበር፤ በእምነቱ ግን በክርስቶስ ዳግም ምፅአት ተስፋ አልቆረጠም፡፡

5. እሷም በጭንቅ ዘመን ትሰራለች ይላል፤ ይሄንን ለመረዳት የህምያን መፅሀፍ ማንበብ ይቀላል እንዴት መቅደሱን ለመገንባት ሲያስቸግራቸው እንደነበር፤ በአንድ እጃቸው የሚገነቡበትን መሳሪያ በሌላ እጃቸው የጦር መሳሪያ ይዘው ነበር፡፡ በዳንኤል 9፥26 ላይ ከ62 ጊዜ 7 በኋላ መሲው ይገድላል ይላል (62x7= 483 ዓመት)

1. መሲው ይገደላል ይላል
2. በእርሱም ዘንድ ምንም የለም
3. የሚመጣውም አለቃ ህዝቡን፣ ከተማውን እና መቅደሱን ያጠፋሉ
4. እስከመጨረሻው ጦርነት ይሆናል፡፡

5. ጥፋትም ተቀጥሯል

ይህ ትንቢት የተለያዩ ቤተክርስቲያናት የተለየ ትርጉም ለመስጠት ቢሞክሩም ይህ ትንቢት የሚያሳየው በ70 AD እንዴት እየሩሳሌም እንደጠፋች የሚያሳይ ነው። ክርስቶስም እየሩሳሌም እንደምትወድም ትንቢት ተናግሮ ነበር፤ ማቴ 24፥1



ዓመት መሲሁ ይገደላል (ከ69 አመት በኋላ)

ዳንኤል ምዕ 9፥27


1. እሱም ከርስቶስ ከብዙዎች ጋር ለአንድ ሱባኤ ሳምንት) ቃል ኪዳን ያደረጋል ዳንኤል 9፥24 ያንብብ ይህ ጥቅስ ስለ ክርስቶስ ስራ የሚያወራ ነው።

    1. ሐጥያትን ይፈፅም ዘንድ
    2. በደልን ያስተሰርይ ዘንድ
    3. የዘላለም ፅድቅ ያገባ ዘንድ
    4. ቅድስተ ቅዱሳኑን ይቀባ ዘንድ
    5. በአህዛብ እና በቅዱሳን ላይ 70 ዓመት ተቆጥሯል (Cut off) ይህ ሁሉ የክርስቶስ ስራ እንደሆነ መፅሀፍ ቅዱስ ያስቀምጣል።

- ✞ ዳንኤል 9፥26 መሲው ይገደላል ይላል
- ✞ ኢሳ 53፥5 ለሀጥያታችን ክርስቶስ እንደቆሰለ ይናገራል
- ✞ 1ጴጥሮ 2፥24 ሀጥያታችን ተሸክሞ ይላል
- ✞ ዳንኤል 9፥27 እንዲቀር አድርጓል

✞ ሉቃ 23፥45 የቤተ-መቅደስ መጋረጃ ተቀደደ፤ ክርስቶስ በሚሰቀልበት ጊዜ፡፡

ዳንኤል 9፥24 70 ዓመት ተቆርጧል ሲል ምን ማለቱ ነው? በዚህ በተሰጣቸው 70 ዓመት ውስጥ አይሁዶችች መመለስ አለባቸው ካልሆነ ግን እግዚአብሔር ይተዋቸዋል፡፡



ዳንኤል 9፥25 ላይ

1. እየሩሳሌም መጠገን እና መሰራት
2. ትእዛዝ ከሚወጣበት ጀምሮ
3. እስከ አለቃው እስከ ሙሴ ድረስ
4. 62 ጊዜ ሰባት ነው ይላል (69 ሳምንት)

   69X7= 483 ዓመት

“ስህተቴን እናዘዛለሁ፤ ተስፋ መቁረጤንም እቀበላለሁ፤ ቢሆንም የጌታ ዳግም ምፅአት ቅርብ እንደሆነ አምናለሁ፡፡ በደጅም እንደቀረበ፡፡”

የሚሊያም ሚለርን ትንቢት አፈታት በመጨረሻ ላይ በተስፋ መቁረጥ ቢጠናቀቅም በጣም ጥቂት ሰዎች ተጨማሪ ጥናት በማድረግ ሚለር የሳተውን አስተካክለዋል፡፡ለዚህም ዋነኛው ሰው ሳሙኤል ኤስ ስኖ ይባላል፡፡

አዲሱ አተረጓጎም

ሳሙኤል ክርስቶስ እንደሚመጣ (እንደሚመለስ) በመደምደም ክርስቶስ የሚመጣው በአስረኛው ቀን በሰባተኛው ወር አክቶቨር 22, 1844 ነው በሚል ጥናቱን አቅርቦ ነበር፤ ግን አሁንም ያ ሳይሆን ቀርቷል፡፡ በ1845 አካባቢ በተለያዩ የሚለራይት እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፈው የነበሩ በማቴ 25፥1-13 ያለውን የ10ቱ ቆነጃጅት ታሪክን አተኩረው ማስተማር ጀምረው ነበር፡፡ መጨረሻ ላይ ንጉሱ ሲመጣ ብዙዎችን እናንተን አላውቃችሁም ብሎ በር ከመዝጋት ጋር አያይዞ (Shut door) ይህ

አተረጓጎም ከምህረት በር መዘጋት ጋር የተያያዘ ነው ብለው ነበር፤ በር ከተዘጋ በኋላ ሌላ ተጨማሪ የምህረት በር የለም፡፡ አክቶቨር 22,
1844 መሰረቱን አጥቷል፡፡

ጆሽዋ ሂምስ (Joshua Himes)

በ1844 ላይ ከነበሩት ሰዎች አንዱ ነበር፡፡ ይህ ሰው በ1844 አክቶቨር ላይ ክርስቶስ አይመጣም ብለው ከተቃወሙት ሰዎች አንዱ ነበር፤ በኋላ ግን በማቴዎስ 25፥1-13 ያለው ትምህርት ተቀብሎ ነበር፡፡ ከታላቁ ተስፋ መቁረጥ በኋላ እየሱስ ሳይመለስ ሲቀር በዛ ቀን በጣም ጥሩ የሆነ ሚና ተጫውቶ ነበር፡፡ክርስቶስ ይመጣል ብለው የሚያምኑትን ሰዎች ሰብስቦ በአፕሪል 1845 በአልባኒያ ኮንፍረንስ (Albany Conference) አድርጎ ነበር፡፡

ይህ ሳይሳካለት ሲቀር ደግሞ የኢቫንጀሊካል አድቬንቲስት መሪ ሆኖ ነበር (Evangelical Adventist) በተጨማሪም አሜሪካ የሚሊኒያል ማህበር አባል በመሆን(1858) ሰንበት ጠባቂዎችን ሲቃወም ነበር፡፡(American Millennial Association) ከቤተመቅደስ ላይ ያላቸውን ማስተዋል እና እውቀት፣ አሁን ያሉበትን ሁናቴና የሚያስተምሩትን ትምህርት ይቃወም ነበር፡፡

ሂራም ኤድሰን (Hiram Edson) 1806-1882

በመጨረሻ ላይ ቤተ-ክርስቲያን የሚለርን ክርስቶስ በ1844 ሲመጣ ይህቺም ምድር በእሳት ትጠፋለች የሚለውን አስተሳሰብ ልክ አይደለም የሚል ውሳኔ ላይ ደርሳ ነበር፡፡ ዳን 8፥14 ያለውን የሚለር አተረጓጎም መጨረሻ ላይ በደረሱበት ድምዳሜ የሰማያዊው ቤተመቅደስ መንፃት ነው ብለው ወሰኑ፤ ምድራዊ ድርጊት እንዳልሆነም ተቀበሉ፡፡
ታዲያ ከነዚህ ከሶስተኛው ከተከፋፈሉት ወይም ከተሰባሰቡት ሰዎች ውስጥ የሰባተኛ አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ተመሰረተች፡፡

ሂራም ኤድሰን (Hiram Edson) ከሌሎች አድቪንቲስቶች ጋር በሚፀልይበት ወቅት እግዚአብሔር በራዕይ ተገልፆለት እንደነበር፤ ለምን እንደዚህ አይነት ትላልቅ ተስፋ መቁረጥ እንዳጋጠማቸው ተብራርቶለት ነበር፡፡ በዚህ ታላቅ ተስፋ መቁረጥ ወቅት ያጋጠሙ ነገሮች መካከል

1. ቤተክርስቲያናት ተቃጥለው ነበር
2. ተዘርፈው ነበር
3. Violence from the Public
4. ብዙ ተከታዮች ተስፋ ቆርጠው ወደ ኋላ አፈግፍገው ነበር

Hiram Edson (የሂራም ኤድሰን አጭር ታሪክ)

1. በኒዮርክ አንቶሪዮ ሃገር ገበሬ ነበር
2. የመጀመሪያ ሚስቱ በ1839 አርፋለች
3. ሶስት ልጆችም አብረው ነበራቸው
4. የሜቶዲስት ቤተክርስቲያን አገልጋይ ነበር
5. ክርስቶስ 1843 ላይ ይመጣል የሚለውን የሚለር ትምህርት ተቀብሎ ነበር፡፡
6. የሚልራይት እንቅስቃሴ ወይም መልዕክት ወደ ኒዮርክ ሮችስታር በ1843 ከዚያም ወደ ፓርት ጊብሰን በቅርብ ጊዜ ተሰራጭቶ ነበር (Rocheste, New york) soon spread to portgibson ኤድሰን ኦክቶቨር 22, 1844 የእየሱስን ዳግም ምፅአት ይጠብቅ ነበር፡፡ እንደ ተጠበቀው እየሱስ ሳይመጣ ሲቀር በጣም ልቡ ተሰብሮ ነበር፡፡ እሱና አንዳንድ ጓደኞቹ በቅርበት የሚኖሩትን የሚልራይት እንቅስቃሴ አባላትን ለመጎብኘት እና ለማበረታታት ሀሳብ አቅርበው ነበር፡፡

   ኤድሰን በበቆሎ ማሳ ውስጥ በሚያልፍበት ጊዜ ነበር ራዕይ ያየው፡፡ የቤተ መቅደስ መንፃት ማለት ክርስቶስ ከቅዱስ ከፍል ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መግባት እንደሆነ በራዕይ ተመልክቶ ነበር፡ ፡

   ኤድሰን ያየውን ራዕይ ለብዙዎች የሚልራይት እንቅስቃሴ ተከታዮች በማካፈል አብራርቶ ነበር፡፡ ይህ የቤተ መቅደሱ ስርዓት በሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት እምነት የፍርድ ምርመራ በመባል ይታወቃል፡፡ ሙሉ በሙሉ አሁን እየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህን ሆኖ በቅድስተ ቅዱሳት ውስጥ ያገለግላል፡፡ ዕብ 4፥14-16

   የዚህ መነቃቃት እስከ 1855 እስኪያበቃ ድረስ ኤድሰን በአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ለብዙ ዓመታት አገልጋይ ሆኖ እየሱስን ቢጠብቁትም ባለመምጣቱ ኤድሰን (Edson) በግል ሰባኪነት አገልግሎት ቀጥሎ ነበር፤ ኤድሰን (Edson) አብሮ ሲሰራ የነበሩት ሰዎች (ጓደኞቹ)

   1. Joseph Bates
   2. Jon Andrews
   3. J-n Loughborugh

ሰንበት ጠባቂዋ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን በ1863 ዓ.ም እንደ ድርጅት ተመስርታለች፡ ፡ ኤድሰን እስከ 1870 ድረስ ህጋዊ አገልጋይ ሆኖ ነበር፡፡

የሰባተኛ ቀን አድቪቲስት ቤተክርስቲያን አባቶች/ፋና ወጊዎች (Pionneers)

የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት አባቶች የምንላቸው የቤተክርስቲያኑ አባል ሆነው በዊሊያም ሚለር እንቅስቃሴ ውስጥ የነበሩ፤ በታላቁ ተስፋ መቁረጥ ውስጥም የነበሩ፤ በኋላ የሰባተኛ ቀን አድቪቲስት እምነትን የመሰረቱ ናቸው፡፡ በ1860 እነዚህ አባቶች የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን የሚለውን ስም ይዘዋል፡፡ የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት የራሷ የሆነ የተለየ እምነት ያላት ሆና በቀን 21,1863 የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ታላቁ ኮንፍረንስ ተመስርቷል፡፡ በመሆኑም እንቅስቃሴ የነበረው አሁን ወደ ድርጅት አድጓል፡፡ ቀደምት አባቶችና ስሞቻቸው **(Pionneers)**

1. Johe Nevins Andrews
2. Joseph Bates
3. John Byengton
4. Daniel T. Bourdeau
5. Merritt Eaton Cornell
6. O.R.L Crosier
7. Hiram Edson
8. John North Lough Borough
9. Uriah Smith
10. Stephen Haskell
11. Ellen G. White
12. James Springer White ….etc

John Nevins Adrews (ጆን ነቪስ አንድሪው)



ጁላይ 22, 1829 ተወለደ

ኦክቶቨር 21, 1883 In bases switzland አድቬንቲስት ሆኗል፡፡ አገልጋይም ሆኖ ነበር፡፡ ፀሀፊና ኤዲተር (Editor) ፣ምሁር (Schalr) የመጀመሪያው አድቪቲስት ሚሽነሪ ነበር፡፡ ከሰሜን አሜሪካ ውጭ በወቅቱ በጣም ሙሁር የሚባል አዋቂ ነበር፡፡ (Author & Scholar) በጊዜው በአድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ካደረጋቸው ነገሮች መካከል

1. የቤተክርስቲያኗን ትምህርት ቀርጿል
2. በራዕይ ዩሐንስ 13 ላይ ያለውን ሁለተኛ አውሬ ሁለት ቀንድ ያለውን ምስል አሜሪካ እንደሆነች በጥናት ደርሶበታል፡፡
3. የቤተክርስቲያንን ህግና ደንብ ፅፏል፡፡
4. በ1855 ባደረገው ጥናት ሰንበት ከአርብ ማታ እስከ ቅዳሜ ማታ እንደሆነ ደርሶበታል
5. ቤተክርስቲያን ህጋዊ የንግድ ድርጅት ውስጥ እንድትገባ እና ነገሮቿን ሁሉ በህግ ማዕቀፍ ውስጥ እንድታገኝ ረድቷታል፡፡ (Legal Business association & allowing the church to obtain legal possession of property)
6. በማተሚያ ቤታችን ውስጥ አገልግሏል
7. ሰንበት እና የመጀመሪያ ቀን የሚል ጥናት አድርጓል
8. በሲውዘርላንድ ወንጌላዊ ሆኖ ነበር፡፡ በዛ የሰንበት ጠባቂዎች ተበታትነው ስለነበር እነሱን በመሰብሰብ ሰርቷል
9. በ54 ዓመቱ በሳንባ ነቀርሳ በመያዝ ከዚህ አለም በሞት ተለይቷል፡፡

ጆሴፍ ቤት



1. ከ15 ዓመቱ ጀምሮ በባህር ላይ ይሰራ ነበር (ካፒቴን ሆኖ)
2. ወደ ተረጋጋ ህይወት የመጣው በ1828 ነው።
3. በታላቁ የአድቬንቲስት እንቅስቃሴ ጊዜ የተከበረ ወንጌላዊ ወይም መንፈሳዊ መሪ ነበር።
4. በ1845 አካባቢ ቤትስ (Bates)በእግዚአብሔር የሰንበትን እውነት አስተውሎ ነበር፤ (የሰባተኛውን ቀን ሰንበትን)
5. በ1846 ዓ.ም 48ገፅ ያለው ስለሰንበት የሚያወራ(የሚናገር) አርቲክል ትንሽ መፅሀፍ ጽፏል
6. 1861 ሚቺጋን በሚባል ግዛት ውስጥ የኮንፍረን ፕሬዝዳንት ሆኖ ነበር
7. ለ80 ዓመት ያህል ኖሯል
8. ለረጅም እድሜ የኖረበት ሚስጥር፣በመልካም ጉልበት እና በጥንካሬ እንዲሁም በመስዋትነት ጭምር ቀላል የአመጋገብ ስርዓት እና እራስን የመግዛት ልምድ ስለነበረው ነው። (Simple Diet and temperance)
9. የመጀመሪያው በአሜሪካ እራስን የመግዛት ማህበር አቋቁሟል። (Temperance Societies)
10. በጣም መንፈሳዊ ሰው ነበር። ነገሮችን በጥራት የሚያስተውል (With Clear Cut View)
11. እንደ አንበሳ ድፍረት የነበረው ሰው ነው (Covrage of Lion)
12. መስዋትነት ለመክፈል አስፈላጊ ከሆነ ወደ ኋላ አይልም ነበር።

Sylvester Bliss (1844-1863)




1. በመጀመሪያ የመጀመሪያው የሚልራይት እንቅስቃሴ ኤዲተር የነበረ ነው፡፡
2. ከዛም የሳይን አፍ ዘ ታይምስ ኤዲተር ነበር፡፡
3. ሊብራል ትምህርት የተማረ ነው (Liberal Education)
4. ታሪካዊ የቦትሰን ማህበር አባል የነበረ (Historical Society of Boston)
5. አድቬንቲስት ሺልድ የተባለው መጋዘን ኤዲተር የነበረ በኋላ በ1853 የሚለር ማስታወሻ የሚለውን እንደ ኤዲተር ሆኖ አገልግሏል፡፡
6. ከስራዎቹ አንዳንዶቹ የራዕይ የሀንስ መጽሀፍ ኮመንተሪ (Commentery) ነው፡፡
7. ህይወቱ እስኪያልፍ ድረስ የአድቬንቲስት ሄራል የሚለውን በኤዲተርነት አገልግሏል (በኋላ ሳይንስ አፍ ዘ ታይምስ የሚለውን መፅሄት) አዘጋጅ ነበር
8. ኮንዲሽናል ኢሞርታሊቲ (Conditional Immortality) የሚለውን ትምህርት እስከ መጨረሻው ካልተቀበሉት የሚልራይት እንቅስቃሴ አንዱ ነበር፡፡

DANLE T BOURDEAU (1835-1905)



1. ወንጌላዊ እና ሚሽነሪ ነበር
2. በ17 ዓመቱ የባብቲስት ቤተክርስቲያን አባል ሆኖ ነበር፤ ፈረንሳይኛ ቋንቋ በሚነገርበት ተቋም ውስጥ ካናዳ ይሰራ ነበር
3. በ1861 አግብቷል
4. በ1858 አገልጋይ ሆኖ በአድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ተቀብቷል
5. በኒው ኢንግላንድ እና በካናዳ እሱ እና ወንድሙ ወንጌላዊ ሆነው አገልግለዋል፡፡
6. ሁለቱ ወንድማማቾች የመጀመሪያዎቹ የፈረንሳይኛ ተናጋሪ ከሆኑ ዘሮች ውስጥ ናቸው፡፡
7. በ1868 በአሜሪካ ካሊፎርኒያ ውስጥ በነበረው ስብሰባ ጥሪ የተደረገለት የመጀመሪያው ሰው ነበር፡፡ ሲመለስ ኤም.ጂ.ኬሎግ በሚመራው (M.G.Kellogg) በአሜሪካ ግዛት ውስጥ ስራ ለመጀመር በ1876 ወደ አውሮፓ ተመልሶ ለአንድ ዓመት በወንጌል ስራ ላይ በሲውዘርላንድ እና በጣሊያን አሳልፏል ከጄ.ኤን.አንድሪው ጋር (J.N.Andrews)በአጠቃላይ 7 ዓመት በውጭ ሃገር አገልግሏል፡፡
8. በ1888 ወደ አሜሪካ በመመለስ በፈረንሳይኛ ተናጋሪ ሰዎች መካከል አገልግሎቱን ቀጥሏል፡፡

John Byington



1. ቨርሞንት (Vermont) በሚባል ቦታ የተወለደ ነው፡፡
2. የሚቶዲስት ሰባኪ ልጅ ነው
3. በ17 ዓመቱ በሚቶዲስት ቤተክርስቲያን የተጠመቀ ነው፡፡
4. በግል እንዲሰብክ ፍቃድ ተሰጥቶት ነበር፡፡
5. ኑሮውን ወደ New York ካደረገ በኋላ በ1877 (Buck's Bridge) ቡክስ ብሪጅ በሚባል ቦታ ባብቲስት ቤተክርስቲያንን ገንብቶ ነበር፡፡
6. ፀረ ባርነት ትግል ውስጥ በጣም ይሳተፍ ነበር፡፡
7. በ1844 የመጀመሪያውን የክርስቶስ ዳግም ምፅአት ስብከት ሰብኳል ትንቢትንም ማጥናት ጀምሮ ነበር፡፡
8. በ1852 ካሪቪው ኤንድ ሄራልድ ላይ በH.W. Lawrence (ኤች. ደብሊው. ላውረንስ) ስለ ሰንበት የሚያወራ ፅሁፍ ደርሶት ነበር፤ ከዛም የሰንበትን እውነት ተቀብሏል፡፡
9. የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያንን ገንብቷል፡፡
10. በ1858 ኤሌንጅዋይት እና ጀምስ ዋይት ወደ ባትል ክሪክ እንዲመጣ ጋብዘውት ነበር፡፡
11. 1863 በ65 ዓመቱ የመጀመሪያው የሰባተኛ ቀን አድቬቲስት ቤተክርስቲያን አለም አቀፍ ፕሬዝዳንት ሆኗል፡፡
12. በሚያገለግልበት ዓመታት በታማኝነት እውነተኛ እረኛ ሆኖ አገልግሏል፡፡
13. ከዚያ ወደ ግብርናው በመመለስ ለ22 ዓመታት በሚቺጋን የሚኖሩትን አማኞች ይጎበኝ ነበር፡፡

Merritt E.Cornell (1827-1893)



ቀጥሎ ነበር ከነዚህ ሰዎች መካከል

✞ Hiram Casc J.H Waggoner James White

1. በኒዮርክ የተወለደ ነው፡፡
2. ከ10 ዓመቱ ጀምሮ የአድቬንቲስትን እውነት ያምን ነበር
3. ለአድቬንቲስት እውነት ህይወቱን ሰጥቶ ነበር፡፡
4. በ1852 የሰንበትን እውነት ተቀብሎ አምኖ ነበር፡፡
5. ወዲያው እንዳመነ የሰንበትን እውነት ለሌሎች ማካፈል ጀምሮ ነበር፡፡
6. ለመጀመሪያ ጊዜ በ1854 ከJ.N.LOUGHBROUGH ጋር በባትል ክሪክ (battle creek) የመጀመሪያውን በድንኳን ውስጥ የሚደረግ የወንጌል ስብሰባ አድርጓል፡፡
7. ከተለያዩ ሰዎች ጋር የወንጌል ጥረቱን
8. በሚያደርገው የወንጌል ጥረት ባለቤቱ አንጀሊና ትረዳው ነበር፡፡
9. በተለያዩ ቦታዎች በመሄድ የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት የምታስተምረውን ትምህርት ይወያይ እና ይከራከር ነበር፡፡
10. እንደ ጴጥሮስ አንዳንድ የባህሪ ችግር ነበረበት፤ ለዛም ኤለንጅ ዋይት መልዕክት ትፅፍለት ነበር፡፡
11. ለ13 ዓመት ያህል ከ1876-1889 ድረስ ተቀናጅተው ወይም ተደራጅተው ከነበሩት ጋር እየሰራ አልነበረም፡፡
12. በ1886 ላይ ለኤለንጅ ዋይት ፅፎ ከልቡ እንደተመለሰ (he deeply repenting man, humbled in the dust") እድሜው ማብቂያ ከ3 ዓመት በፊት እንደገና ወደ አገልግሎት ተመልሶ ነበር፡፡

Owen Resell Loomis Crosier (1820-1913)



1. የሚልራይት እንቅስቃሴ ሰባኪ ነበር፡፡
2. ከሂራምራ ኤድሰን ጋር ይሰራ የነበረ ነው (Hiram Edson) እና ከ Dr. F.B (ዶክተር ኤፍ. ቢ. ሃን) ትናንሽ በራሪ ወረቀቶችን ለሚልራይት እንቅስቃሴ ያትም ነበር፡፡
3. በዚያን በታላቅ ተስፋ መቁረጥ ቀን በኦክቶበር 22, 1844 ከኤድሰን ጋር አብረው ነበሩ፡፡
4. ኤድሰን (Edson) ከእግዚአብሔር መንፈሳዊ ማብራሪያ ካገኘ በኋላ ለምን ክርስቶስ ኦክቶበር 22, 1844 ላይ እንዳልመጣ ነገር ግን ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ እንደሚገባ ተረዳ
5. Crosir, Edson and Hahn ቤተ መቅደሱን አብረው ከሚያጠኑት መሀል ነበሩ
6. Crosir ተመርጦ ነበር፤ ስለ ቤተ መቅደሱ እና እንዴት መቅደሱ እንደሚነፃ የጥናታቸውን ውጤት በጽሁፍ እንዲያቀርብ ተጠይቆ ነበር፡፡
7. Joseph Bates (ጆሴፍ ቤትስ) እና James White በተፃፈው ፅሁፍ በጣም ልባቸው ከተነካባቸው ሰዎች መካከል ነበሩ፡፡
8. ኤለን.ጂ ዋይትም Dark-Star Extra ተብሎ በተፃፈው ፅሁፍ ላይ በ1846 ላይ እንደ እውነተኛ ብርሃን እዩት ብላ ነበር፡፡ (True Light)
9. Elder Bates ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ሰንበት ፅውነት ለሁሉም በሚያቀርብበት ጊዜ በመጀመሪያ በመቀበል ሰንበትን መጠበቅ ጀምሮ ነበር፡፡
10. በሚያሳዝን ሁኔታ ሰንበት መጠበቅንም ሆነ ስለ ሰማያዊ ቤተ መቅደስ የነበረውን አመለካከት እርግፍ አድርጎ ትቶት ነበር፡፡
11. ምንም እንኳን ምንም አይነት አስተዋፆ ባያደርግም የቤተ መቅደሱ ስርዓት ትምህርት እስከ አሁን የቤተክርስቲያኑ ትምህርት ሆኖ ቀጥሏል፡፡

12. የደህንነት እቅድ በትክክል እና በሚያምር ሁኔታ ሙሴ በገነባው መቅደስ ውስጥ በደንብ ተገልፆ እናየዋለን፡፡


Charles Fitch (1805-1844)



1. በኮንግሬሽናል (Congregational Church) ቤተክርስቲያን ነው አገልግሎቱን የጀመረው፡፡ በማርች 1833 ለዊሊያም ሚለር የርሱን ትምህርት አንብቦ እንደነበር ደብዳቤ ፅፎለት ነበር፡፡
2. የዊሊያም ሚለር ትምህርት ትክክል እንደነበር አልተጠራጠረም
3. የቅድስና ወንጌል ሰባኪ ነው፤ ካለበት ቤተክርስቲያን መለየት እንዳለበት ተገንዝቦ ነበር፡፡ የሚልራይትን ትምህርት በማስተዋሉ ይህ ደግሞ ብዙ ተፅኖ የማይፈጥር ሰው ሊያደርገኝ ይችላል ብሎ አስቦ ነበር።
4. Josjar Litch የሚባል ሰው ከምታስተምረው የቅድስና ትምህርት ጋር የክርስቶስን ሁለተኛ መመለስ መጨመር አለብህ ብሎት ነበር
5. ብዙ ፅሁፎችን እንዲያጠና ትቶለት ሄዶ ይህ ጥናት የክርስቶስን ዳግም ምፅአት ትምህርት እንዲያምን እረድቶታል፡፡
6. Litch ያለ መታከት ሰዎች ለክርስቶስ ዳግም ምፅአት እንዲዘጋጁ እየዞረ ይስበክ ነበር
7. በ1842 ቻርት መስራት እንዳለበት ተሰምቶት ነበር በዚህ ምክንያት ታዋቂ የሆነውን የመጨረሻውን ዘመን ትዕይንት የሚያሳየውን እና የዳንኤል ትንቢት አፈፃፀም የሚያሳየውን ቻርት ሰርቷል።
8. በሚልራይት (Mille rites) እንቅስቃሴ የነበሩ ሰዎች በሚገባ ይህንን ይጠቀሙበት ነበር
9. Fiter እርሱ እራሱ የዳንኤልን ምዕራፍ ሁለትን ቻርት ይጠቀምበት ነበር

10. በ1844 ላይ በኒሞኒያ ታሞ ነበር ምናልባት ሲያጠምቅ ብርድ አግኝቶት ይሆናል፡፡
11. ሰኞ አክቶበር (October) 14 ላይ አርፏል (ሞተ) በሙሉ እምነት ከጥቂት ጊዜያት በኋላ እንደ ጌታችን ክርስቶስ አንዱ ቀን ይነሳል

Stephen is Haskell



1. ወንጌላዊ እና አስተዳዳሪ ነበር
2. በኒው ኢንግላንድ (New England) በ1853 ሰንበት ጠባቂ ላልሆኑ አድቬንቲስቶች ይሰበክ ነበር፡፡
3. በዛው ዓመት ሰንበትን መጠበቅ ጀመረ
4. በ1870 በመቀባት የኒው ኢንግላንድ ኮንፍረንስ (New England Conference) ፕሬዝዳንት ሆኖ ነበር
5. በ1870 የመጀመሪያው የኮንፍራንሱን ትራክት አዘጋጀ
6. የተለያዩ ሚሽነሪዎችንም ወደ ተለያዩ ምስራቅ የአሜሪካ ግዛቶች ይልክ ነበር፡፡
7. ሶስት ጊዜ የካሊፎርኒያ ኮንፍረንስን ፕሬዚዳንት ሆኖ ነበር
8. ሶስት የመፅሀፍ ቅዱስ አስተማሪዎችን በመያዝ በኢንግላንድ እና በእንግሊዝ የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ስራን ጀምሯል
9. በ1885 ወደ አውስትራሊያ እና ኒውዝላንድ የተለያዩ ሰዎች ይዞ በመሄድ ስራውን ይመራ ነበር፡፡

10. ከ1889-1890 የወንጌል ሰራተኞችን በመወከል አለማቀፋዊ ጉዞ አድርጎ ነበር ።።
11. የጎበኛቸው ሃገሮች ምዕራብ አውሮፓ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ኢንዲያ፣ ቻይና፣ ጃፓን እና አውስትራሊያ ናቸው።
12. ለመጀመሪያ ጊዜ በ1902የአፍሪካ አሜሪካን የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን በኒዮርክ ከተማ መስርቷል
13. እራስን መግዛት ትምህርት በ Maine (በሚኒ) በሚባል ቦታ በ1911 ጀምሮ ነበር
14. በ1912 ለአይነ ስውራን መፅሀፍ ማተም ጀምሮ ነበር
15. የኤለን.ጂ.ዋይት መታሰቢያ ሆስፒታልን ለመገንባት ያስተባበር (ይረዳ) ነበር White Memorial Hospital. በ1916 የፃፋቸው መፃህፎች
    - ✞ The Story of Daniel the prophet
    - ✞ The story of seer of Patmos
    - ✞ The Cross and it's shadow



John Norton Lough Brorough (1832-1924)

1. ሰንበት ጠባቂ የሆነው በJ.N Andrews ስራ አማካኝነት ነው፡፡
2. ወዲያው ነበር መስበክ የጀመረው በ1854 ዓ.ም የተቀባ አገልጋይ ሆኖ ነበር፡፡
3. ከD.T Bordeanu ጋር በመሆን የመጀመሪያ ሚሽነሪ ሆኖ ነበር ወደ ካሊፎርኒያ የሄደው ::
4. (ኢሎሞይ የሚባል ቦታ) ወደ አውሮፓም ሄዶ Pillipols ኮንፍረንስ መሪ ሆኖ ነበር
5. የአድቬንቲስ ቤተክርስቲያን የመጀመሪያው ታሪክ አዋቂ ነበር፣ መፅሐፍም ፅፎ ነበር፡፡
6. “The Rise and Progress of SDA and the Great Second Coming Advent Movement” የሚል መፅሐፍ ፅፏል፡ ፡
7. በፅሁፍ ወንጌልን ለማስተላለፍ በጣም ፍላጎት የነበረው ሰው በመሆኑ እሱ እና James White (ጀምስ ዋይት) እንዴት አድርገው የወንጌልን ስራ ማስፋፋት እንደሚቻል ይመክሩ ነበር፡፡
8. በጥቂት ዋጋ ፅሁፎችን ማቅረብ የሚል ሃሳብ አቅርበው የነበረ ሲሆን ይህም ጥሩ ውጤት አምጥቶ ነበር፡፡ በመሆኑም ይህ መንገድ ብዙ ፅሁፎች እንዲፃፉ አድርጎ ነበር፡፡
9. ይህ ሰው በጣም ጥሩ የነበረ የእምነት ጀማሪ ሲሆን ብዙ ችሎታውን ለዚህ መልዕክት መስፋፋት ያበረከተ ሰው ነው፡፡
10. ይህ ሰው ለሰማያዊ ራዕይ በጣም ታዛዥ የነበረ በመሆኑ እግዚአብሔር የእሱን እውነት ለማስተላለፍ የተጠቀመበት ሰው ነበር፡፡
11. በ1924 April በ92 ዓመቱ በሰላም አርፏል፡፡

William Miller (ዊሊያም ሚለር)




1. ጥሩ የሆነ ሀይማኖታዊ ታሪክ የነበረው ነው፤ ነገር ግን ከተሳሳቱ ሰዎች ጋር ገጥሞ ስለነበር ነገሮች ተበላሽተው ነበር፤ ስለ እግዚአብሔርም የተሳሳተ አመለካከት ነበረው፡፡
2. በ34 ዓመቱ ያለው አመለካከት ስላላረካው መንፈስ ቅዱስ መፅሀፍ ቅዱስን እንዲያጠና ገፋፍቶት ነበር፤ በክርስቶስ አማካኝነት መልስ ለሚያስፈልገው ነገር አግኝቶ ነበር፡፡
3. ዊሊያም ሚለር ያደረገው ጥናት ወደ መጀመሪያው እና ሁለተኛው የክርስቶስ ዳግም ምፅአት መርቶት ነበር፤ የራዕይ ዩሀንስ መፅሀፍት እና የዳንኤል መፅሐፍት በጣም ማርከውት ነበር፡ ፡
4. በ1818 ዓ.ም የዳንኤል 8 እና 9 የጥናቱ ውጤት ክርስቶስ በ1844 ላይ ወደዚህ ምድር ይመለሳል ወደሚል ወደ አንድ መደምደሚያ ላይ አድርሶት ነበር ፡፡
5. እስከ 1831 ድረስ በመጠራጠር እውነቱን ሳያስተላልፍ ቀርቶ ነበር፡፡
6. ከ100,000 ሺ ሰዎች በላይ በክርስቶስ ዳግም ምፅአት አምነው ነበር፡፡
7. በ1849 ዓመተ ምህረት አርፏል (ሞቷል)

8. እግዚአብሔር ሰዎችን ለክርስቶስ ዳግም መፅአት (ለፍርድ ምርመራ እንዲያዘጋጅ) ተጠቅሞበት ነበር፡፡

Thomas M. Preble

ቶማስ ኤም ፕሬብል



1. የባብቲስት እምነት አገልጋይ የነበረ(Baptist) እና የሚልራይት ሰባኪ ነበር፡፡
2. በ1844 አጋማሽ ላይ የሰንበትን እውነት ተቀብሎ ነበር
3. የመጀመሪያው አድቬንቲስት ሰባኪ ነበር ስለ ሰንበት ጽሁፍ/መጽሀፍ እንዲታተም ያደረገ (የቀሰቀሰ) ሰው ነው
4. የእስራኤል ተስፋ በሚል በየጊዜው የሚታተም መፅሄት እንዲታተም አድርጓል (an Adventist periodical of Portland, Maine of February 28, 1845)
5. ይህ ህትመት ለጆሴፍ ቤት(Joseph Bates) የሰባተኛ ቀን ሰንበትነት እንዲደረሰው ወይም እንዲያወቅ ረድቶታል።

Uriah Smith (1832-1903)

ዩሪያ ስሚዝ



1. በዲሴምበር 1852 በሰንበት ጠባቂ አድቬንቲስቶች ተምሮ ነበር፤ ለረጅም ጊዜ ለሪቪው እና ሄራልድ ኤዲተር ሆኖም አገልግሏል፡፡
2. በ1863 ስሚዝ ለጀነራል ኮንፍረንስ ሴክረቲሪ ሆኖ አገልግሏል።
3. የዳንኤል እና የዩሐንስ ራዕይን መፅሀፍ በመፃፍ በመፃፍ ይታወቃል፡፡
4. በባትል ክሪክ (Battle Creek) የመጀመሪያው መፅሀፍ ቅዱስ አስተማሪ ነበር፡፡
5. ስሚዝ በህፃንነቱ ባትል ክሪክ በነበረበት ወቅት (Battle Creek) እግሩ ተቆርጦ ስለነበር ደረጃ ለመወጣት በጣም ይቸገር ነበር።
6. በሚሰራበት በር ላይ እንዲህ ብሎ ፅፎ ነበር
   - Editor's Room
   - Busy? Yes always It you have any business Attend your business.
     Let's attend to our business

7. ስሚዝ ሁል ጊዜ ለጌታ ሰራ የሚሮጥ በመሆኑ በጌታ ስራ በጣም የተጠመደ ነበር፣ ሰዎች እራሳቸውን እንዲሆኑ ይፈልግ ነበር፡፡ በጣም ደግ እና ልበቅን ሰው ነበር፡፡

Ellen.G.White




1. ኤ.ጂ.ዋይት እና ቤተሰቦቿ በ1840 በሜቶደስት ካምፕ ሚቲግ ላይ እያሉ ነበር የተለወጠችው፤ ከዚያ ከሁለት ዓመት በኋላ ተጠምቃለች፡፡
2. የአድቬንቲስት ሰዎች ወደ ሰማይ የሚያደርጉትን ጉዞ በተመለከተ ፤ በዲሴምበር 1844 ላይ የመጀመሪያውን ህልም አይታለች
3. የትዳር አጋሯን ጀምስ ዋይትን (James White) Feb 1845 ላይ አግኝታ አገስት 1846 ላይ ደግሞ አግብታዋለች፡፡
4. የመጀመሪያ የጋብቻ አመቶቻቸው በጣም በችግር፣ በከባድ ስራ እና በድህነት የተሞላ ነበር።
5. በ1849 ኤለን.ጂ.ዋይት የእግዚአብሔር ጥሪን ተከትሎ ጀምስ ዋይት የህትመት ስራ እንዲጀምር አድርጋ ነበር፤ የመጀመሪያውም መፅሔት ፕሬዘንት ትሩዝ የሚል ነበር (Present Truth)
6. በግል ለተለዩ ሰዎች መልዕክት የምትሰጠው ህልም እና ራዕይ ተቀብላ ነበር፤
7. በመፅሀፍ ቅዱስ ወቅትን የሚያመላክቱ የተለያዩ አርዕስቶች ላይ በደንብ ፅፋ ነበር ።
   - በክርስቶስ እና በሰይጣን መሀከል ያለውን ተጋድሎ በተመለከተ
   - ስለ ትምህርት
   - ስለ ጤና
   - ስለ ቤተሰብ ከፃፈቻቸው ጥቂቶቹ ናቸው ።
8. አማኞች እነዚህ መልዕክቶች ተመርኩዘው ፣ ትምህርት ቤቶች፣ ማተሚያ ቤቶች እንዲሁም Sanitariums ከፍተዋል፡፡
9. ለብዙ ዓመታት ለዚህ ስራ እራሷን አሳልፋ ሰጥታ የነበረ ሲሆን፤ በነዚህ ዓመታት ውስጥ የፅድቅ በሀይማኖትን ትምህርት በጣም አጉልታ ታስተምር ነበር፡፡
10. እነዚህን መልዕክቶች ሰዎች በማይቀበሉበት ወቅት ያለውን አደጋ አስቀምጣለች፡፡
11. የመጨረሻ ዓመቶቿን ያሳለፈችው በካሊፎርኒያ ነበር፤ በጣም በአስቸጋሪ ጊዜያት ቢሆኑም እግዚአብሔር እስከመጨረሻው ተጠቅሞባት ነበር፡፡ ቤተክርስቲያንን

በመውቀስ፣ በመምራት፣ በማስተማር፣ ሀጥያተኞችን ወደ ክርስቶስ በመምራት ግልፅ በሆነ መንገድ ሰዎችን ለክርስቶስ ዳግም ምፅአት እንዲዘጋጁ ማድረግ ችላለች፡፡

James Springer White (1821-1881)

ጀምስ ስፕሪንገር ዋይት



1. በመጀመሪያ አስተማሪ ነበረ፤ በኋላም የሚልራይትን እንቅስቃሴ በመቀላቀል ክርስቲያን ሆኗል በመሆኑም የእየሱስን ዳግም ምፅአት ተቀብሎ የተዋጣለት ሰባኪ ሆኗል፡፡
2. በጣም ድንቅ መክሊት ያለው እና፣ የመምራት ብቃት የነበረው በጣም ነበዝ ሰባኪ ነበር፤ የተዋጣለት የ7ኛ ቀን አድቬቲስት ሐዋሪያ ነበር፡፡
3. ጀምስ ዋይት የመጀመሪያውን ፕሬዘንት ትሩዝ የሚለውን በየጊዜው የሚወጣውን ፅሁፍ ጀማሪ ነበር፤ ሪቪው ኤንድ ሄራልድ የሚለው መፅሀፍ ኤዲተርም ነበር፡፡

✞ ያገለገለባቸው መስኮች

1. Present Truth (1849)
2. Review and Herald (1850)
3. Youth instructor (1852)
4. Signs of the times.

4. የጀነራል ኮንፍረንስም ፕሬዝዳንት ሆኖ አገልግሏል (1865-1867)፣ (1869-1871) እና 1874-1880
5. የሪቪው እና ሄራልድ መስራች ጀምስ እና ሚስቱ ኤለን.ጂ.ዋይት ነበሩ።
6. አገስት 1881 ዓመተ ምህረት ሞቷል፡፡ የሞተውም በስራ ብዛት ነበር ::
7. ያሳለፈው የ60 ዓመት ህይወት ራስ ወዳድ ባለመሆን እና በመስዋትነት ነበር ::

8. ከሰባተኛ ቀን አድቬንትስት አገልጋዮች ውስጥ እንደ ጀምስ ዋይት ያለ ከፍተኛ የሆነ ብቃት ለቤተክርስቲያን ህይወት እንዲሁም ለድርጅቷ አስተዋጽኦ ያደረገ አልነበረም፡፡

Alongo T. Jones (1850-1923)



1. በ20 ዓመቱ በውትድርና አገልግሏል
2. በሚገርም ሁኔታ ብዙውን ጊዜ የሚያጠፋው ታሪካዊ በሆኑ ስራዎች ላይ፣ በሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት የህትመት ስራዎች ላይ እና በመፅሀፍ ቅዱስ ላይ ነበር፡፡
3. ልክ ውትድርናውን እንደለቀቀ መስበክ ጀመረ፤ በ1885 የሳይንስ አፍ ዘታይምስ አዘጋጅ ሆኖ ነበር፡፡ (Editor) በኋላ ላይ E.J.Waggner ተቀላቅሎት ነበር፡፡
4. በ1888 እነዚህ ሁለት ሰባኪዎች የጀነራል ኮንፍረንስን በሚኒፖሊስ የተደረገውን ፅድቅ በሀይማኖት ስብከት አነቃንቀውት ነበር፤ ከዚያ በኋላ ለብዙ ዓመታት ይሄን ትምህርት ይሰብኩ ነበር፡፡ ኤለን.ጂ.ዋይትም ከጎናቸው ነበረች፡፡
5. ኤለን ዋይት በJones (በጆንስ) ስብከት የተመለከተችው ነገር “በጣም ድንቅ የሆነ የእምነት እና የክርስቶስ የፅድቅ ትምህርት፣ የክርስቶስ የብርሃን ጎርፍ” ብላ በመጽሐፏ ገልፃዋለች፡፡ (E.G.W 1888 Matrials, P123)
6. በ1889 ከ J.O.Corliss ጋር በመሆን የእሁድ ህግን በተመለከተ በአሜሪካ ኮንግረስ ቀርበው ተቃውመው ነበር፡፡ከዚያም በኋላ ታዋቂ የሆነ የእምነት ነፃነት ተከራካሪ የነበረ ሲሆን ፤የሀይማኖት ነፃነት የሚል መፅሄት አዘጋጅም (Editor) ነበር፡፡
7. በአንድ ወቅት (1901-1903) የካሊፎርኒያ ኮንፍረንስ መሪ ሆኖ ነበር፤ ከዶክተር J.H.Kellogg’s ጋር አብሮ እየሰራ ኤለንጅ ዋይት የፃፈቻቸውን ምክሮች በመቃወም በመጨረሻ ሰዓት ላይ የተሳሳተ እና ጥበብ ያልተሞላበት ውሳኔ በመወሰን ከቤተክርስቲያን አባልነቱ ራሱን እስከ ማጣት ደርሶ ነበር፡፡

8. Jones እስከ መጨረሻው ድረስ ስለሰንበት እውነት እና ለአንዳንድ የቤተክርስቲያኗ ትምህርቶች ታማኝ ነበር፤ የፅድቅ ሀይማኖትን ትምህርት በማስተዋወቅ በቤተክርስቲያኗ ምንጊዜም ይታውሳል፡፡

Dr. Ellet J.Wagner /ዶ/ር ኤሌት ጄ ዋግነር /



1. በ1844 ረዳት የሳይት አፍ ዘ ታይምስ አዘጋጅ ነበር፤ ከአባቱ ጋር በመሆን አገልግሉዋል
2. ከሁለት ዓመት በኋላ A.T Jones በተመሳሳይ መፅሄት ላይ አብሮ መስራት ጀመረ፡ ፡ ዋግነር እስከ 1891 ድረስ በተመሳሳይ ቦታ ላይ ሰርቷል
3. በ1888 እሱ እና ጆንስ (Jones) ታዋቂ የነበረውን የፅድቅ በሀይማኖት ትምህርት በጀነራል ኮንፍረንስ ስብሰባ ላይ በሚኒሶታ ሚኒ ፖሊስ በተደረገው ስብሰባ ላይ አቅርበው ነበር፡፡
4. ፕሬዘንት ትሩዝ ለሚባለው መጽሄት አዘጋጅ ሆኖ ነበር፡፡ በኢንግላንድ (England) እስከ 1902 ድረስ ኖሯል፡፡
5. ወደ አሜሪካ ከተመለሰ በኋላ አማኑኤል ሚሽነሪ በሚባል ኮሌጅ ውስጥ ሰርቶ ነበር (Emmanuel Missionary College)
6. ትዳር ላይ ባጋጠመው ችግር ተፋቶ ሌላ ሚስት በማግባቱ ከቤተክርስቲያኗ ስራ ላይ ተነስቶ ነበር፤ አንዳንድ ሰዎች ስለ ጽድቅ በሀይማኖት ላይ ያመጣውን መልዕክት በትዳር ላይ ባጋጠመው ችግር ምክንያት ሳይቀበሉ ቀርተው ነበር፤ ኤለን ዋይትም በጠላት ወጥመድ የሚገባ ከሆነይህ ፈተና እንደሚሆን አስጠንቅቃው ነበር።
7. በዚህ ሰውዬ ላይ ምንም እንደዚህ ያለ ነገር ቢከሰትም እንኳን “I see the beauty of the truth in the presentation” of the righteousness of Christ in relation to the low as the doctor has placed it before us” MS 15 1888

“ዶክተሩ ያቀረበውን ከህግ ጋር ተያይዞ ስለ ክርስቶስ ፅድቅ ያቀረበውን ውበቱን አይቻለሁ” MS 15 1888

“እግዚአብሔር ይሄን መልዕክት እንዲያውጅ ሸክም ሲሰጠው ‹ቃላት በማይገልፀው ሁኔታ እግዚአብሔርን አመስግኜ ነበር፣ ለወቅቱ የሚያስፈልግ መልዕክት እንደሆነ አውቄያለሁ›፡ ፡”ብሏል። MS 24 1888

William Warren Prescott

ዊሊያም ዎርን ፕሪስኮት



1. አስተማሪ እና አስተዳዳሪ ነበር
2. ቤተሰቦቹ በኒው ኢንግላንድ ከሚልራይት እንቅስቃሴ ጋር አብረው ነበሩ
3. በ1877 ከ Dartmouth Collage ተመርቋል።
4. ቨርማውንት (Vermont) በሚባል አካባቢ አስተማሪ እንዲሁም የመፅሄት አዘጋጅ ነበር።
5. 1885-1894 የባትል ክሪክ ኮሌጅ ፕሬዝዳንትነት ተቀብሎት በዛ እየሰራ ባለበት ወቅት የዩኒዮን ኮሌጅ (Union Collage) እንዲመሰረት ረድቷል። በ1892 ‹የዋላ ዋላ ኮሌጅ› ፕሬዝዳንት ሆኗል (Walla Walla Collage)

መፅሀፍ ቅዱስን በደምብ ያውቅ ስለነበር በተለያዩ የአለም ሃገራት ጉዞ ያደርግ ነበር።

6. ‹የጀነራል ኮንፍረንስ› ፕሬዝዳንት ሆኖ ነበር፤ እንዲሁም ‹የሪቪው ኤንድ ሄራልድ› (Review and Herald) አዘጋጅም ነበር።
7. በ1915 አንስቶ እስከ 1937 ጡረታ እስኪወጣ ድረስ የጀነራል ኮንፍረንስ ሴክረቴሪ ነበር፤

(Secretary of the General Conference) W.W Prescott was also in the 1890's said to be one of "the lord's chosen messengers, beloved of


God" who had

"Co-Operated with God in the word for this time"

(The 1888 Ellen G. White Materials, P, 1241)

God gave him "a special message for the people" which he gave "in demonstration of the spirit and power of God" (E.G.W. Review and herald, January 07, 1896)

Gorge Storrs



በ19 ዓመቱ የሜተድስቲን ቤተክርስቲያን ተቀላቀለ፡፡ በብዛት ስለ ባርነት ይሰብክ ስለነበር በ1835 ታስሮ ነበር፡፡ ስለ ፀረ-ባርነት ስብሰባ በሚደረግበት ጊዜ ከፍርድ በኋላ ነፃ ወጥቷል፡፡ በ1837 ሙታን ያሉበትን ሁኔታ የተፃፈ ትራክት አንብቦ የነበረ ሲሆን፣ ይህ ፅሁፍ የሜቱድስቲን ቤተክርስቲያን እንዲለቅ እረድቶታል፡፡ በዚያ አመት በሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያንን መልዕክት ሰምቶ ስነበር በዚያው አመት መስበክ ጀመረ፡፡ነገር ግን እስኪሞት ድረስ የቤተመቅደሱን መልዕክት አልተቀበለም ነበር፡፡ በሚል ራይት እንቅስቃሴ የተሰበከውን እንዲሁም የሰንበት እውነት አልቀበለም፡፡ ነገር ግን መፅሀፍ ቅዱስ ስለሙታን የሚያስተምረውን አልካደም ነበር፡፡

ዳንኤል 12፥1

እንደ ዳንኤል 7፥2 /ዮሀ 13፤5/ ዮሀ ራዕይ 11፥3 ዘመን ዘመናት የዘመን እኩሌታ፤42 ወደ የሚለው እና 1260 የሚለው ሁሉ ተመሳሳይ የትንቢት ክስተቶች ናቸው፡፡

<u>በተለየ መንገድ ሲገለፅ ደግሞ</u>

- ✞ ይህ ጳጳሳዊ ስርአት 1260 የእግዚ/ር ሰዎች ሲያሳድድ ሲገድል እና ምድርን በጨለማ ውስጥ እንድትወድቅ ያደረገበት ጊዜ ነበር፡፡
- ✞ መጽሀፍ ቅዱስ መያዝ ወንጀል የሆነበት ወቅት ስለነበር የጨለማ ዘመን በመባል ይታወቃል፡፡
- ✞ ትንቢተ ዳንኤል 7፥25 ዘመን (አንድ ዓመት), ዘመናት (ሁለት ዓመት) የዘመን እኩሌታ (ስድስት ወር)
- ✞ ዮሀንስ ራዕይ 11፥3 ➐1260 ዓመት
- ✞ ዮሀንስ ራዕይ 13፥1 ➐ 42 ወር =(42x30 =1260)
- ✞ 1260 = የመጀምርበት 538 AD ነው
  - 1798 ሙሉ በሙሉ ስልጣኑን ጳጳሳዊ ስርአት ያጣበት ወቅት ነበር፡፤ ይህውም በፈረንሳይ ጀነራል ተማርኮ ወደ ግዞት የሄደበት ወቅት የካቶሊክ ቤተ/ክ ሙሉ በሙሉ ሀይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ ስልጣንን ያጣበት ወቅት ነው፡፡
  - ትንቢተ ዳንኤል 8፥14 1843 (1844) የ2300 ትንቢት የሚፈፀምባ ወቅት ነው፡፤
  - 457 = እየሩስአሌም ቅጥሮቿ መሰራትና መጠገን የጀመረበት ወቅት ነው፡፡
  - 2300-457 = 1843 AD

1290 =

የዘውትር መስዋአት የቀረበት የጥፋት እርኩሰት የቆመበት ነው፡፡ ይህ ማለት ከሰማይ የተሰጠውን የደህንነት ትምህርት በመተው ሰው እንዴት አድርጎ

በሰራው መዳን እንደሚችል ብሎም የተሳሳቱ ትምህርቶች በተለይ በሮማን ካቶሊክ ቤተክርስትያን አማካኝነት የገባበት ወቅትን ያመላክታል።።

ምሳሌ- ህፃናትን ማጥመቅ፣ በተለያዩ ቅዱሳን በሚሉዋቸው ማመንን፣ ሰው ለዘላለም እየተቃጠለ ይኖራል የሚሉ እና ሌሎች በርካቶች መጽሀፍ ቅዱስ የማይደግፋቸው ትምህርቶች ገብተዋል።።

1335 = እስከ 1335 ቀን ምስጉን ነው።።

እንደ ትንቢተ ዳንኤል 12፥13 ሰዎች <u>በመጨረሻ ዘመን</u> መፅሀፍን እንደሚመረምሩ ከዚያም እንደሚያስተውሉ ይናገራል፤ መፅሀፉን ዝጋ እስከ ዘመን መጨረሻ ድረስ።።

ትንቢተ ዳንኤል 12፥9-10

ዳንኤል 12፥4

- እስከ ፍፃሜው ዘመን ድረስ መፅሀፉን ዝጋ ቃሉን አትም ይላል

  ይህ ማለት የትንቢተ ዳንኤል መጽሀፍ የሚስተዋለው በዘመን መጨረሻ ነው።። ይህን በአይምሮአችን ውስጥ እንደያዝን፡

- በዳንኤል 12፥6 የዚህ ድንቅ ፍፃሜ እስከመቼ ነው ይለዋል።። በዳንኤል12፥7 ላይ የተቀደሰው ህዝብ ሀይል መበተን ከተፈፀመ በኋላ ነው።።

- ዘመን ዘመናት ለዘመን እኩሌታ (1260 ዓመት የሚያሳይ ነው።። 1798 የዚህ 1260 ዓመት ትንቢት 1798 AD የመጨረሻው ዘመን የሚጀምርበት ወቅት ነው።። መጽሀፍ ቅዱስ ይህን ያስረዳል።።

  ስለዚህ

1. የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት የተነሳችው ከ1798 ዓ.ም በኋላ ነው።።

   1798 AD

   <u>-1290</u> AD ❼ የዘውትር መስዋት የቀረበት

   508 AD ❼ ጳጳሳዊ ስርዐት የጀመረበት ወቅት ነው።። (ሙሉ ስልጣን ያገኘበት ወቅት)

   (ዳንኤል7፥25,ዮሀራዕይ 13፥5, ዮሀንስ ራዕይ11፥3)

   1335 AD ❼ 1335 የሚታገስ ምስጉን ነው (ትንቢተ ዳንኤል 12፥12)

+508 AD

1843 AD ➐ የ2300 ዓመት ትንቢት የተጠናቀቀበት ክርስቶስ ከቅድስት ክፍሉ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የገባበት ወቅት ነው፡፡

የ2300 ትንቢተ ዳንኤል 8፥14 ላይ ይገኛል፡፡

- 2300-457 = 1843 /457 BC የ2300 ትንቢት የሚጀምርበት ወቅት ወይም መነሻ ነው፡፡
- 457 እየሩሳሌም የመጠገን እና መሰራት ትዕዛዝ የወጣበት ወቅት ነው፡፡
- ክርስቶስ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የፍርድ ምርመራውን ለመጀመር የገባበትን ጊዜ ነው፡፡ ለአንድ ሺ ሶስት መቶ አምስት ጊዜ የሚታገስ የሚለውን ስንቀንስ ጳጳሳዊ ስርአት የተነሳበትን ወይም ፖለቲካዊ እና ሀይማኖታዊ ስልጣን ያገኘችበትን ጊዜ ያደርሰናል፡፡ በቁጥር ስናስቀምጥ

1843 AD

-1335 AD

508 AD

ይህ ትንቢት የሚያሳይን የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤ/ክ በመጨረሻው ዘመን ያስነሳት ብቸኛ የቤ/ክ መሆኑን ያረጋግጥልናል፡፡ በሌላ አነጋገር የእግዚ/ር ቤ/ክ ናት ማለት ነው፡፡ የዚችን የሰባተኛ ቀን ቤ/ክ ሙሉ በሙሉ ታሪኳን ከአነሳስ እስከመጨረሻ ድረስ የሚያሳየውን የሚቀጥለውን መጽሀፍ ህትመት በፀሎት እና በትእግስት ይጠብቁ፡፡